# ጋሽ ኮሎኔል አብዮት

ከጌትነት

ጋሽ ኮሎኔል ልፍስፍሱ
ሕዝብን በደም ያስለወሱ

በረንቲቻ አባ ድቤ
አፈ ቅቤ ልበ ጩቤ

ነገ ሴራ ዛሬ ፉፋ
ማሰናዶ ለጠለፋ

ሩዋንዳን ለመድገም
ላይ ታች የምያዘግም

የአዛኝ ቅበ አንጓች አጬብርባሪ
ዘረኛ ማሰሪ

ኮሎኔል ምነው እየገለፈጡ
በምስኪኑ አርሶአደር ባያላግጡ

እያዘዙ ማሮጥ የለሁም ለማለት
ነገ ወዴት ይሆን ጉዞ ያቀዱበት ?

በሰፈሩት ቁና መሰፈሩ ላይቀር
ከቶ ለምን ይሆን በከንቱ መሽቀርቀር

ህዝብ እንባው ይጎርፋል
የቤት ፍርሻው ድግስ ሞቅ ሞቁ ደርቷል
አገሬን ለማረስ ሴራው ተሸምቋል
በእንዲህ ያለ ጊዜ በእንዲህ  ያለ ዘመን አይተኙም የነቋል!!

10.04.2019